ጥር 2 8 2012
4/0476/12

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission

የገ/ዘ/133??
2012-5-12

በዝርዝሩ ለተመለከቱት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

የገቢ.ዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1.0/124/12 ጥር 21 ቀን 2012 በተጻፈ ደብዳቤ የውጭ ድርጅቶች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመጠቀም በመንግስት የተለዩ ሸቀጦችንና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተሰጠውን አቅጣጫ ልኳል፡፡

በመሆኑም የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ30-5/732/15 ጥር 19 ቀን 2012 በተጻፈ ደብዳቤ የውጭ ድርጅቶች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመንግስት የተለዩ ሸቀጦችንና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም እያሳሰብን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳወቀበትን 04 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መንግስቱ ተፈራ አያና
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር/
ተወካይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission

ግልባጭ

- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ

ጉምሩክ ኮሚሽን

- ለታክስ እና ጉምሩክ መረጃ፣ ማብራሪያ እና ምክር አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ገቢ.ዎች ሚኒስቴር

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  አዲስ አበባ
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሞጆ
- ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  አዳማ
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ድሬዳዋ
- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ጅግጅጋ
- ለሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሀዋሳ
- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ጅማ
- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሞያሌ
- ለአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  አዋሽ
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ጋላፊ
- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ኮምቦልቻ
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  መቀሌ
- ለባህርዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ባህርዳር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን ጥር 2 1 2012
Date
ቁጥር 1-0/124/12
Ref.No

ለጉምሩክ ኮሚሽን
ለሕግ ተገዥነት ማስከበር ዘርፍ
ለሀገር ውስጥ ታክስ
<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

ጉዳዩ፡- <u>የውጭ ድርጅቶች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመንግስት የተለዩ ሸቀጦችንና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን ይመለከታል፡፡</u>

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በቁጥር መ30-5/732/15 ጥር 19/2012 ዓ.ም ለሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን በጻፈው ደብዳቤ የውጭ ድርጅቶች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመንግስት የተለዩ ሸቀጦችንና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን በተመለከተ 3 ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ተስፋዬ ቱሉ መልካ
ሚኒስቴር ጽ/ቤት ኃላፊ

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
**የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት**

Federal Democratic Republic of Ethiopia
**OFFICE OF THE PRIME MINISTER**

ቀን/Date: 19 ጥር 2012
ቁጥር/Ref. No. ጠ/ሚ50-5/732/15

ለገንዘብ ሚኒስቴር

ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ለገቢዎች ሚኒስቴር

ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡-የ<u>ዉጭ ደርጅቶችከራሳቸዉ የዉጭ ምንዛሪ ምንጭ በመንግስት የተለዩ ሸቀጦችንና የኢንዱስትሪ ግበአቶችን ወደ ሀገር ዉስጥ ስለማስገባት፡-</u>

መንግስት ሀገሪቱ ለጊዜዉ የገጠማትን የዉጭ ምንዛሪ ዕጥረት ለመቋቋም እንዲያግዝ የዉጭ ድርጅቶች ሆነዉ ሸቀጦችን/ግበአቶችን ወደ ሀገር ዉስጥ ካስገቡ በኋላ በጊዜ ሂደት ሊከፈላቸዉ በሚገባ መልኩ የራሳቸዉ የዉጭ ምንዛሪ በመጠቀም በመንግስት የተለዩ/የሚለዩ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግበአቶችን ወደ ሀገር ዉስጥ እንዲያስገቡ አቅጣጫ ማስቀመጡ ይታወቃል፡፡

መንግስት ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ቦርድ በዉጭዉ አለም ከፍተኛ ልምድ ያላቸዉ የዉጭ ድርጅቶች ከራሳቸዉ የዉጭ ምንዛሪ ምንጭ የሚፈልጉ ሸቀጦች እና የኢንዱስትሪ ግብአቶች ወደ ሀገር ዉስጥ እንዲገቡ ፈቅዷል፡፡በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የተሰጠዉን ዉሳኔ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለዉ መልኩ ስራ ላይ ለማዋል ስራዉን በባለቤትነት የሚመሩ በተዋረድም በአፈፃፀሙ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑ ተቋሞችን የስራ ድርሻ የለየ የአፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ስልክ/Tel.: +251 111 241 214
ፋክስ/Fax: 226 292
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box: 1031

ኢትዮጵያ፡ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ
Ethiopia: A New Horizon of Hope
@PMEthiopia @PMoEthiopia

በዚህም መሠረት:-

1) <u>የገንዘብ ሚኒስትር</u>

1.1. ለአፈጻጸም እንዲረዳ በመንግሥት የተለዩ/የሚለዩ ሸቀጦች እና የኢንዱስትሪ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ መመሪያ ያዘጋጀል፡፡

1.2. ሸቀጦች/ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ያመቻቻል፡፡

2) <u>የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

2.1. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦችን/የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ይለያል መጠኑን ይወስናል

2.2. ሸቀጦችን/የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ለማቅረብ የሚፈልጉ ድርጅቶች የፍላጐት መግለጫ (expression of Interest) እንዲያቀርቡ (ውክልና) ጥሪ ያደርጋል፣ አጭር የአቅራቢዎች ዝርዝር (short list) የማወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ (RID) በማዘጋጀት አሸናፊውን ይለያል፡፡ውል ያዋውላል አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

2.3. ተወዳዳሪዎቹ ላቀረቡት ሸቀጥ/ግብዓት በጊዜ ሂደት ክፍያቸው በውጭ ምንዛሪ ሊተላለፍላቸው (repatriate) የሚገቡ ድርጅቶችን ይለያል ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ መቼና ስንት መሆኑን የሚያመለክት መረጃ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

2.4. ሸቀጦቹ/የኢንዱስትሪ ግብዓቶቹ ወደብ ወይም ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ስለሚሠራጭበት ሁኔታ አፈጻጸም ሥርዓት ይዘረጋል፣.... ወዘተ

3) <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ</u>

3.1. ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚቀርብለት መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለአስመጪ ድርጅቶቹ ሊተላለፍ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ በወቅቱ እንዲልክ ይፈቅዳል፣

3.2. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት ካጋጠመው ከራሱ ክፍያ እንዲፈጽም ያደርጋል፡፡

4) <u>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ</u>

4.1. ለአስመጪዎቹ የውጭ ምንዛሪ እስኪተላለፍ በአስመጪ ኩባንያዎች ስም ሂሳብ ይከፍታል፡፡

4.2. አስመጪዎቹ በገቡት ውል መሠረት ገንዘባቸውን በውጭ ምንዛሪ እንዲከፈላቸው በሚፈለግበት ጊዜ ገንዘብ ያስተላልፋል፡፡

5) <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>

5.1. ሸቀጦችን/ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ከሽያጭ የሚገኘውን ገቢ መልሶ ለኢንቨትስመንት ለማዋል ለሚፈልጉ ድርጅቶች ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

6) <u>የገቢዎች ሚኒስቴር</u>

6.1. ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚተላለፍት መሠረት ዕቃዎቹ እንደአስፈላጊነቱ ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፣

6.2. የጉምሩክ ፎርማሊቲ በተፋጠነ ጊዜ ውስጥ እንዲፈጸም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ስለዚህ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው መመሪያ እና ለየተቋማቱ በተቀመጠው ኃላፊነት እና የሥራ ድርሻ መሠረት በውድድር የተመረጡት ድርጅቶች/ ኩባንያዎች የተፈቀዱ ሸቀጦች እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ፣እንዲሠራጩና በተገባው ውል መሠረት በውጭ ምንዛሪ የማስተላለፉ ተግባር እንዲፈጸም መታዘዙን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
Office of the Prime Minister

ደሚቱ ሐምቢሳ ቦንሣ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊና
የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር